# ይሉሃል (ይሉሻል) ይኼ ነው



ከሕያው ቃል

በእዳ ተገድግዶ፣ አጽሙን የቆመ ካብ፣
መለሰኛዉ ርቆ፣ ተደግፎ ርብራብ፣
ደመና የጠቀሰ፣ በነፋስ ምሕረት የተገተረ ግምብ፤
ከሰገነቱ ላይ፣ በዘር የከበረ፣ ባንክ ያጭበረበረ፣
በሙስና አቋራጭ፣ በቅርብ የቶጀረ፤
የሥርዓት ደላላ፣
ባለአራት ኮከብ፣ የውሸት አባዱላ፣
ቁልቁል በመሳለቅ፣ በጉንዳኑ ፍጥረት፣
በትዕቢት፣ በንቀት፣ ቆሞ 'ሚያፏጭበት፤
ብድር ካነጠፈው፣ ቀለበት ምቹ አስፋልት፤
ጥንቢራዉ የዞረ፣
የደደበ ካድሬ፣
ጠግቦ እያበሰና "ፏ ዶጁ" 'ሚልባት፤
ደግሞ ቤት ሲገቡ፣ ባለቀለም ምትሃት፣
የምድር ጎስቋላዎች፣ ጠግበው የሚያድሩበት፣
መጢቃ ትዕይንት፤
የሚያሽቃብጡበት፣ የቧልት ሙዚቀኞች፣
የሚያንቋልጡበት፣

በ'ርቃን ቀረሽ ግልድም፣ ጉደኛ ዳንሰኞች፣

አገሩን አፍርሶ፣ መንደሩን አባባይ፣

ነጻነትን ገድሎ፣ "ለመብትህ ልሙት" ባይ፣

በቅይጥ አንደበት፣

ቱልቱላ ዲስኩሩን፣ ቆሞ 'ሚያናፋበት፣

የብዙሃን ዕጦት፣ የደልቃቆች ጥገት፤

ይሉሃል ይኼ ነው!

ይሉሻል ይኼ ነው!

የወያኔ ሕዳሴ - የወያኔ ልማት።

መስከረም 2004 ዓ. ም.